## ይድረስ ለፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም

## እስከመቸ አደገኛ ሽማግሌ?

ልክ የዛሬ 10 ዓመት በፊት (መጋቢት 1990) በጦማር ጋዜጣ "የዳግመኛ ፋኖ ተሰማራ የተቀደደ ነጋሪት " ብለው ለፃፉት አስተዛዛቢ ፅሁፍ "ከዝቅጠቱ ቀነስ" ብዬ በፃፍኩልዎ መልስ የእንግሊዙ ደራሲ ጆርጅ በርናርድ ሾው "ሽማግሌዎች አደገኞች ናቸው ስለቀሪው ዓለም ግድ የላቸውምና" ያለውን ጠቅሼሎት አባክዎ አደገኛነትዎ ያብቃ ብዬዎት ነበር። ግን መስሚያ ጆሮ ሊያገኙ የ ሉ አይመስሉም። ወያኔ ለስልጣን ከመብቃቱ በፊትና ከዚያም በኋላ በአፍራሽ ጎዳና፣ በተለይም የሕዝብን ትግል ጎድቶ ለጨቋኞቹ በሚረዳ መልኩ ሲፈራጡና ሲዳዙ ታይተዋል። በግንቦት-ሰኔ 1997 እርሶን ጭምር መሪ ብሎ ህይወቱን የሰጠውን ዜጋ ሁሉ ጭፍን አድርገው ክደው በቅርቡ ደግሞ ለወያኔ ተገዙ፣ በወያኔ ላይ ብረት አታንሱ፣ እኛ አለአነሱ እነሱም አለእኛ መኖር አንችልም፣ "ልጆቹ ተምረዋል"፣ የቃሊቲንና የመቃብር ጉድጓድን በር እየከፈቱ ቢያስቸግሩም ክንችር አድርገው የዘጉትን የዴሞክራሲ በር ይከፍታሉ፣ ወዘተ በሚል ትጥቅ አስፈቺና ትግል ገዳይ ሰበካዎን ተያይዘውታል። ሽማግሌ በምክሩ አርበኛ በሰናድሩ ይገል የነበረውን ዛሬም ተቃውመው ዕድሜ ሽክምና ከንቱ እንድንል ገፋፍተውናል። የዛሬ ልፈፋዎን እርቃኑን ለማስቀረትና ስልፍዎ ፀረ ሕዝብ መሆኑን ለማሳየት የዛሬ አስር ዓመት የፃፍኩልዎ ምላሽ ዛሬም ስለሚሰራ ከዚህ ቀጥዬ በስፋት አቀርበዋለሁ።

" በቅድሚያ ልገልፅልዎ የምፈልገው ጉዳይ በእርስዎ " መላ ወይስ ዱላ" ፅሁፍ የተጀመረው እሰጥ አገባ የወያኔን ልብ እያሞቀ ያለ ክስተት መሆኑን በማመኔ በክርክሩ ላልገባ ምዬ አሁን ግን የእርስዎ አፍራሽ ሚና ዝምታን ተፃራሪ ሆኖብኝ መፃፍ መገደዴን እንዲያውቁልኝ ነው። በበኩሌ ከዚህ በፊት አንድ ተቺ እንዳልዎት የእርስዎ አዳናቂ አይደለሁም። በዱሮ ዘመን ሳውቅዎት በዴሞክራትነት ሳይሆን በሌላ፣ በሰላማዊነት ሳይሆን በደጅ ጠብቀኝ ባይነት፣ በአርበኝነት ሳይሆን በአፍቅሮ አሜሪካ የሚታወቁ ነበሩ። ደርግ ጊዜም ሚናዎን ያውቁታል፣ እኛም አልዘነጋንም። ደርግ ሊወድቅ ሲል ከበርኒንገሀም ከተማ ለንደን መጥቼም እነ መለስን ሲያዳንቁና ከእነ አብዱልና እንድርያስ እሸቴም ጋር ሽርጉድ ሲሉ ታዝቤዎታለሁ። ይህን ሁሉ የማትተው ከእርስዎ ብዙ የጠበቅኩ ሰው አልነበርኩም ልልዎት ነው።

ወደ ቁምነገሩ ለመመለስ፣

በፅሁፍዎ ሁሉ የሰፈረው ተጨምቆ የሚያሳየው ፍፁም የተለየ ሀሳብን የመቻል ልምድም ችሎታውም እንደሌለዎት ነው። በእርግጥ ስለመቻቻልና ሀሳብ ስለመለዋወጥ መገል ያለበትን ይላሉ--መባል ስላለበት ብቻ!! ዴሞክራት አይደሉም። ያ ያረጁበት አፍቅሮ አሜሪካ አገርሽቶ ያጋልጦታል።...የ እርስዎ መነሻ ቁምነገር ወያኔን በትጥቅ አትፋለሙ፣ትጥቅ ትግል የሚሉትን አትስሙ አትከተሉ የሚል ነው። አፃፃፍዎና የክርክርዎ ይዘት ለወያኔ ዘብ የቆሙ የሚያስመሰልብዎ ና በትጥቅ የታገሉትንና እየታገሉ ያሉትን ስም ለማጥፋት፣ለማጉደፍ፣ ውጉዝ ከመ አርዮስ ለማሰኘት የሚያረጉት ጥረት ነው። ታሪክን ይበርዛሉ፣ያጣምማሉ፣የማይገባ ነገር ደግሞ ይዋሻሉ። በሰላም እንታገል ብሎ በቀና ይህንኑ ሀሳብ ማስተላለፍ ሲቻልና ሲገባ ሌሎችን የታገሉና እየታገሉ ያሉትን በመዝለፍ ( ትችትዎ ገንቢና ስነ ስርዓት ያለው ሳይሆን አዋራጅ በመሆኑ) ወደዱም ጠሉም ወያኔን ይረዳሉ። በታሪክ ወሳኝ ማጠፊያዎች ላይ የእርስዎ አቅዋም ሁሌም አወዛጋቢ ሆኖ ያለው በዚህ መልክ ነው። የሕዝብ ጎራን በውዥንብር ያተራምሳሉ።...

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ለተቺዎችም ሲመልሱ ያቺው እኔ “ወንድ” አንተ ፈሪ--ደጅ ጠብቀኝ--ይሏት የነበረችው ልምድ ብቅ ትላለች። ሁሉንም--አጼ ኃይለስላሴንም ሳይቀር-- በስደተኝነት ያክቸለችላሉ። እኔ ጀግናው ሳልሰደድ በሀገር አለሁ፤ እታገላለሁ፤ ጀግና ነኝ አጨብጭቡልኝ፤ የሚል ይመስላል ፅሁፍዎ። በቅድሚያ የተሰደደ ፈሪ ያልተሰደደ ጀግና ብሎ መደምደም እንደማይቻል ላሳስብዎ። ከዚያ ደግሞ ታዳጊ ያላት በግ ላትዋን ደጅ አሳደረች ሲባሉም ይቻላል። ስንቱ ሲታሰር፤ ታስሮ ደብዛው ሲጠፋ፤ስንቱ ሞትን በስደት ሲያመልጥ እርስዎ አልታሰሩም፤መውጣት መግባት አልተከለከሉም። ለምን ብለን እንጠይቅ ? ታዳጊ? የወረቀት ነብር? አሰላለፍ? ሊረዱ እንደሚችሉት ይህ ዓይነቱ ጉዳይ ለውይይት አይጠቅምም። በውጭ ያለው ኢትዮጵያዊ ፈሪ ወይ ትግል የሸሸ አይደለም። ይታረሙ።------ ልጆች ለጦርነት መዳረጋቸውንም--ከባድ ጥያቄና ዓለም አቀፋዊ ችግር ሆኖ ሳለ --ለከለልተኛ የፖለቲካ ንትርክ ተጠቅመውበታል። በነገራችን ልጆቻችንን እንዳይመለምሉብን ዘብ ቆመን ነበር ላሉት የእርስዎን ልጆች በተመለከተ ሊከሱት የፈለጉት ድርጅት ሊመለምልም አልቃጣ ነበር ማለት ይቻላል። ( ምናልባት አባታቸውን በአማካሪነት ያሰራ የነበረው ሰደድ ሞክሮ ይሆን?!)። በትግሉ ወቅት እርስዎ ብቻ ሳይሆኑ እኛም አዲስ አበባ ነበርንና የነበረውን ሁኔታ እናውቀዋለን። ወቀሳ አግባብ ባለው መልክ ሲቀርብ ጠቀሜታ አለው። የራስን የሳደፈ ሚና ለመሸፋፈኛ ሲውል ግን ፋይዳቢስ ሆኖ ይቀራል።......ህዝባችን ማን ወንጀለኛ ማን ንፁህ እንደሆነ ያውቃል። ይጠየቅ ሲባል ደግሞ ማን በዝባዥ ስርዓትን እንደታገለ ማን ከወቅቱ ኢምፔሪያሊስት ሀገር ጋር ተፋቅሮ ጠብቅና እንደቆመ ፤ ማን አረመኔ ወታደራው ቡድንን እንደታገለ ማን ደግሞ ለሕዝብ ስልጣን እንዳትሰጡ እያለ እንደመከረ ፤ማን ወያኔን እንደተቃወመ ማን ወያኔን ልጆቼ ብሎ በኮኸን አቅራቢነት እጅ እንደነሳና ተቃዋሚዎቻቸውን እንዳክቸለቸለ ሕዝብ ይፈርዳል። ስለዚህ ብዙ አይድከሙ። ሀገርና ፍትህ ይኑሩ እንጂ ማን ሕዝብን እንደሚፈራ ያኔ የሚታይ ይሆናል።

ጥያቄው ሀገር እንዴት ትኑር ነው። ለዚህ ምላሻቸውን ሕይወታቸውን በመሰዋት እየሰጡ ያሉ አሉ። ፕሮፌሰር ሰላም ሰላም እያሉ ይሰብካሉ። ይሁንልዎ። በሆነማ ማን ሞትን ጦርነትን ፈልጎ። መንገዱን እስቲ ያሳዩን እርሶወም። ሌላውን መዝለፍ ሳይሆን ይኸው የተሻለ መንገድ ብለው በአርአያነት ያሳዩ። ደፋር ጀግና ሆነው በቦታው እስካሉ ድረስ። እኛ ፈሪዎቹን ስደተኞቹን ይተዉን። ጠመንጃ ያነሱት በሀገር ያሉት መስሎን ወይስ ለእርስዎ ከአዲስ አበባ ውጪ ባዕድ ሀገር ነው?... ትግል የሚያካሂዱት ክፍሎች ለስልጣን በሚል አሉታዊ መልክ ያቀርባሉ። መስዋዕት የሚከፈለው የማንንም ጎፈሬ ለማበጠር አይደለም። ትግል ለስልጣን ነው። ለማን ሥልጣን ነው የሚለው ነው ዋናው ጥያቄ።...... ፕሮፌሰር ታሪካችንን አያበላሹብን፤ ትግላችንን አያኮላሹብን፤ታሪክ እንደገና ልትታዘብዎት አይገባም። ደፈረኝ አይበሉና ጭራሽ አላማረብዎትም። ”

ይህን የፃፉክልዎ ከ 10 ዓመት በፊት ነው። ከዚያ ወዲያ ምን ሲያደርጉ ታዩ? የያዙት ዛር አልለቅ ብሎ በአፍራሽነት ትግል ሲጎዱ ከረሙ። አንዳንዶች--ብጤዎችዎ- ሰሞን በአዎንታዊ እያነሱ ቢዘምሩም በትግሉ ውስጥ ሚናዎ ጎጂ ሆኖ ቀጥሏል። ገርበብ አለ ያሉት በር የዴሞክራሲሰ ሮይሆን የከርቸሌና ቃሊቲ በመሆኑ ከብጤዎችዎ ና ድርጅትን ዛሬም እያፈረሱ ካሉት ጋር ዘብጢያ ወረዱ። መታሰሩ ትምህርት አልሆንዎትም። ቅንጅት ብለው ትግል ብለው ለጋ ህይወታቸውን የለገሱትን እነ ሽብሬንና ሌሎችንም ለመርሳትና ለመካድ ጊዜ አልፈጀብዎትም። ከባዕዳንና ተመሳጥረውና ቡከኖችን ቀደም ቀደም አድርግው የሕዝብን ትግል አዳፈኑ፤አስጠቁ። አልበቃ ብሎ ዛሬም በዚሁ ቀጥለውበታል። የማሳብደድ ፕሮፌሰር፤ የክህደት ፈላስፋ፤ አደገኛ አዛውንት። ቅንጅቱን ለማፍረስ በተሸረበው ሴራ ግንባር ቀደም ሆነውና በግንባር ቀደም አደናጋሪነት የምትሰለፍ ግለሰብን ይዘው እነሆ ቅንጅትን ለማፍረስና አንጃዎን ለወያኔ ለማስገዛት ደፋ ቀና እያሉ ነው። በሰላም ትግል ሽፋንም ፀረ ወያኔ ትግልን ሁሉ ለማፈን እየጮሁ ነው። አለ እኛ አይኖሩም፤ቀና ትምህርት ተምረዋል ብለው የሕዝብና የሀገር ጠላቶችን ወዳጅ

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

አድርግው ሳያፍሩ እየሰፈፉ ነው። ለነገሩ ነፍሰ ገዳዩን ክንፈ ገብረ መድህንን ወዳጄ ብለው የቆዩ አልነበሩም? መጥኔ ቅሌት!!

ሁሌም በትግል ወሳኝ ወቅቶች በትግል እሳት ላይ ውሃ ያፈሳሉ። ድርግ ስልጣን ከህዝብ ሲቀማ ሚናዎን ይረሳሉ? መንግስቱ ራሱ እስረኞችን ግደሉ ምክር በእርሰዎ ተሰገሰን አሳሳም? ወያኔ ስልጣን ሲይዝ ሲልስ ከእን አብዱል አባቦራና እንድርያስ እሸቴ ጋር ሆነው የሰጡት ድጋፍና ፀረ ወያኔዎችን የሰደቡትስ? የትጥቅ ትግሉ ሲፋፋም ሲልስ መሳ ወይስ ዱሳ ወዘተ ብለው የጮሁትና ደንቃራ ለመሆን የጣሩት? የአሁኑስ ፀረ ቅንጅት፤ ፀረ ትግል ፤ ፀረ ትጥቅ ትግል ኡኡታዎና ሻጥርዎ? ዛሬ ግን ተነቅቶቦታልና ብዙም አያደናግሩም።

ዛዲያ አደገኛ ሽማግሌ ብልዎት ያንስዎታል?

በለጠ ታደሰ ነኝ

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com